# ትንቢተ ፡ ዐብድዩ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## ትንቢተ ፡ ዐብድዩ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1

1 ፤ የዐብድዩ ፡ ራእይ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኤዶምያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ ሰምተናል ፤ መልእክተኛ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ተልኮ ፦ ተነሡ ፥ በላይዋም ፡ በሰልፍ ፡ እንነሣ ፡ ብሏል ።

2 ፤ እንሆ ፥ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ታናሽ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ አንተ ፡ እጅግ ፡ ተንቀኻል ።

3 ፤ በተሰነጠቀ ፡ አለት ፡ ውስጥ ፡ የምትኖር ፥ ማደሪያኽንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረግኽ ፥ በልብኽም ፦ ወደ ፡ ምድር ፡ የሚያወርደኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የምትል ፡ አንተ ፡ ሆይ ፥ የልብኽ ፡ ትዕቢት ፡ አታሎኻል ።

4 ፤ እንደ ፡ ንስር ፡ መጥቀኽ ፡ ብትወጣ ፥ ቤትኽም ፡ በከዋክብት ፡ መካከል ፡ ቢኾን ፥ ከዚያ ፡ አወርድኻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

5 ፤ ሌባዎች ፡ ቢመጡብኽ ፡ ወይም ፡ ወንበዴዎች ፡ በሌሊት ፡ ቢመጡ ፥ የሚበቃቸውን ፡ የሚሰርቁ ፡ አይደሉምን ፧ ወይንንም ፡ የሚቈርጡ ፡ ወዳንተ ፡ ቢመጡ ፡ ቃርሚያ ፡ አያስቀሩምን ፧

6 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ምንኛ ፡ ጠፋኽ! ዔሳው ፡ ምንኛ ፡ ተመረመረ! የተሸሸገበት ፡ ነገር ፡ ምንኛ ፡ ተፈለገ!

7 ፤ የተማማልኻቸው ፡ ሰዎች ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ ዳርቻኽ ፡ ሰደዱኽ ፤ የታመንኻቸው ፡ ሰዎች ፡ አታለሉኽ ፥ አሸነፉኽም ፤ በበታችኽም ፡ አሽክላ ፡ ዘረጉብኽ ፥ እነርሱም ፡ ማስተዋል ፡ የላቸውም ።

8 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከኤዶምያስ ፡ ጥበበኛዎችን ፥ ከዔሳውም ፡ ተራራ ፡ ማስተዋልን ፡ አላጠፋምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ ቴማን ፡ ሆይ ፥ ሰዎች ፡ ዅሉ ፡ ከዔሳው ፡ ተራራ ፡ በመገደል ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ኀያላንኽ ፡ ይደነግጣሉ ።

10 ፤ በወንድምኽ ፡ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ስለ ተደረገ ፡ ግፍ ፡ ዕፍረት ፡ ይከድንኻል ፥ ለዘለዓለምም ፡ ትጠፋለኽ ።

11 ፤ በፊቱ ፡ አንጻር ፡ በቆምኽ ፡ ቀን ፥ አሕዛብ ፡ ጭፍራውን ፡ በማረኩበት ፥ እንግዳዎችም ፡ በበሩ ፡ በገቡበት ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዕጣ ፡ በተጣጣሉበት ፡ ቀን ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ነበርኽ ።

12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመከራው ፡ ቀን ፡ ወንድምኽን ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይልኽ ፡ ዘንድ ፥ በጭንቀትም ፡ ቀን ፡ በትዕቢት ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ፡ ነበር ።

13 ፤ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በሕዝቤ ፡ በር ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ መከራቸውን ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በሀብታቸው ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ ትዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ፡ ነበር ።

14 ፤ የሸሹትንም ፡ ለመግደል ፡ በመንታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ትቆም ፡ ዘንድ ፥ በጭንቀትም ፡ ቀን ፡ ከርሱ ፡ የቀሩትን ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ፡ ነበር ።

15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ በአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ቀርቧልና ፤ አንተ ፡ እንዳደረግኸው ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግብኻል ፥ ፍዳኽም ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ ይመለሳል ።

16 ፤ በቅዱስ ፡ ተራራዬ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጠጣችኹ ፡ እንዲሁ ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ዘወትር ፡ ይጠጣሉ ፤ አዎን ፡ ይጠጣሉ ፥ ይጨልጡማል ፥ እንዳልኾኑም ፡ ይኾናሉ ።

17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የሚያመልጡ ፡ ይኾናሉ ፥ ርሱም ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናል ፤ የያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ ርስታቸውን ፡ ይወርሳሉ ።

18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተናግሯልና ፥ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ እሳት ፥ የዮሴፍ ፡ ቤት ፡ ነበልባልም ፥ የዔሳው ፡ ቤት ፡ ገለባ ፡ ይኾናሉ ፤ እነርሱንም ፡ ያቃጥሏቸዋል ፡ ይበሏቸውማል ፤ ከዔሳውም ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ የለውም ።



www.ethiopianorthodox.org

19 ፤ የደቡብም ፡ ሰዎች ፡ የዔሳውን ፡ ተራራ ፥ የቈላውም ፡ ሰዎች ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ይወርሳሉ ፤ የኤፍሬምንም ፡
አገር ፡ የሰማርያንም ፡ አገር ፡ ይወርሳሉ ፤ ብንያምም ፡ ገለዓድን ፡ ይወርሳል ።

20 ፤ ይህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የጭፍራቸው ፡ ምርኮ ፡ የከነዓንን ፡ ስፍራ ፡ ኸሉ ፡ እስከ ፡ ሰራጵታ ፡ ድረስ ፡
ይወርሳል ፤ በስፋራድም ፡ የሚኖሩ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ምርኮኛዎች ፡ የደቡብን ፡ ከተማዎች ፡ ይወርሳሉ ።

21 ፤ በዔሳውም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ አዳኞች ፡ ወደጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፤ መንግሥቱም ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ይኾናል ፨



www.ethiopianorthodox.org